

ከተስፋዬ ዘነበ (ኖርዌይ በርገን) 26/10/2012

# <u>ማን ይሆን ያንቺ ልጅ ?</u>

የሶስት  ሺህ ዘመን ሃገር፣

የቤሄሮች ጥምር ህብር፡፡

ብዙ ኖረሽ፣

ትንሽ ያጣሽ፣

ከፊት ቀድመሽ፣

ኋላ ቀረሽ፡፡

ጥሪትሽን አሟጠሽ ያስተማርሺው ልጅሽ፣

ውለታሽን  እረስቶ ሲዶልት ካራጅሽ፡፡

ገላሽን በልቶ ለባህድ ሲሸጡሽ፣

የምን እርግማን ነው የወጣው ከሆድሽ፡፡

ይህው ታነቢያለሽ አምናና ካቻምና፣

ባንዳ ልጆች ወልደሽ የሚነሱሽ ጤና፡፡

ይህው ታነቢያለሽ ወልደሽ መራር ፍሬ፣

ጥቂቶች ሆነውሽ የቀን ለሊት አውሬ፡፡

የቱ ይባል ያንቺ የአብራክሽ ክፋይ፣

ለንቺ ሲል የኖረ ውለታሽን ከፋይ፡፡

እኮ የቱ ይሆን የኔ የምትይው፣

የትውልድ አደራ  ጠብቆ ያቆየው፡፡

መቼም በዚህ ዘመን  አጋም አብቅለሻል፣

ለቅሶሽም በርክቶ  ጠቁረሻል ከስለሻል፡፡

ስንቶቹ ለክብርሽ እንዳልተሰዉልሽ፣

ጥቂቶች ሊያፈርሱሽ ከተት አወጁብሽ፡፡

ለክብርሽ ሞግተው ተው አይሆንም ያሉ፣

በብረት ተገፍተው ከሃገር ኮበለሉ፡፡

ህብር ቀለምሽን ልዩነት አርገውት፣

የአንድ እናት ልጆችን በዘር ከፋፍለውት፣

መዘውሩን ይዘው ወዝውዘው በተኑት፡

የሁሉ እናት ሆነሽ ሁሉን አንድ ያደረግሽ፣

ከሃዲ ልጅ ወልደሽ መከራሽን አየሽ፡፡

የቱ ይባል ያንቺ የአብራክሽ ክፋይ፣

ለአንቺ ሲል የኖረ ውለታሽን ከፋይ፡፡

እኮ የቱ ይሆን የኔ የምትይው፣

የትውልድ አደራ ጠብቆ ያቆየው፡፡

አንቺማ ምን ታረጊ ሚዛንሽ እኩል ነው፣

ሁሉም ባንቺ ትንፋሽ ሞቆ ነው ያደገው፡፡

ግና በአንቺ እድሜ በዘመንሽ

ለማን ከፍተሽ፣

ማንን ታደግሽ፡፡

የትኛው ነው ያንቺ እንቁ፣

ከዚህ ሁሉ ከደቂቁ፡፡

የትኛው ነው ላንቺ ክብር የወደቀ፣

ደግሞስ የቱ ባንቺነቱ የፀደቀ፡፡

እኮ ስንቱ

ለአንቺ አርማ

ለአንቺ ድንበር፣

እሱ አልፎ ሆነሽ ክብር፡፡

የቱ ይባል ያንቺ የአብራክሽ ክፋይ፣

ለንቺ ሲል የኖረ ውለታሽን ከፋይ፡፡

እኮ የቱ ይሆን  የኔ የምትይው፣

የትውልድ አደራ ጠብቆ ያቆየው፡፡

አይዞሽ ኢትዮጲያዬ ትንሳኤሽ ተቃርቧል፣

በህብር ልጆችሽ ታሪክ ይቀየራል፣

ሰንጎ የያዘሽ መዥገርሽ ይወድቃል፡፡

ይሰማል ቅዳሴ ይሰማል አዛኑ፣

ይህ እኩይ ስርዓት ሲወርድ ከዙፋኑ፡፡

በህብረት ቆመዋል ዘር እምነት ሳይለዩ፣

ከፋፋይ ጉጅሌን ፍዳውን ሊያሳዩ፡፡

የቱ ይባል ያንቺ  የአብራክሽ ክፋይ፣

ለንቺ ሲል የኖረ ውለታሽን ከፋይ፡፡

እኮ የቱ ይሆን  የኔ የምትይው፣

የትውልድ አደራ ጠብቆ ያቆየው፡፡

## ድል ለኢትዮጲያ ህዝብ!!!!

## ሞት ለወያኔና ለሆዳሞች!!!!

ለአስተያየቶ፡-ftih_lewegen@yahoo.com

(Ethiocenter.blogspot.no)